# ድንቄም ተቃዋሚ

ዳግም ላይፋቱ ፡ በተክሊል ተጋቡ
ጉሮ ወሸባዬ ፡ አጨብጭበው ገቡ
ወንበር እያሞቁ ፡ ቁጭ ብለው ፡ ያራግቡ
ለምን እንደ ሕዝቡ ፡ ይጠሙ ይራቡ?
ይሰፈርላቸው ፡ የደም ብር ፡ ቀለቡ ፡፡

ሙሽሪት ልመጂ ፡ ሙሽሪት ልመጂ
ወዳንቺ የሚመጣ ፡ አልክ አማላጅ
ከወያኔ መንደር ፡ የለም ያገር ልጅ
የደም ዕዳ አለበት ፡ አዲሱ ወዳጅ
በራስሽ ቀልደሽ ፡ በሰው አትቀልጅ ፡፡

ያብርሃም የሳራ ፡ ይሁን ጋብቻችሁ
ተደርድሮ አየነው ፡ የሰርጉ ዋንጫችሁ
በደም የተሞላው ፡ የክደት ጽዋችሁ
መቼም ፡ ታጥቦ አይጸዳ ፡ ቆሽሿል እጃችሁ
ተጨማለቁበት ፡ ፍርድ እስኪሰጣችሁ ፡፡

በግንቦት ፡ ሰርግ አናውቅ ፡ እኛ ባገራችን
ከጥንት ያልነበረ ፡ የለ ከወጋችን
አድርጉ ይሉናል ፡ አለ ባህላችን
ስርአትን ማፍረስ ፡ የለም በደማችን ፡፡

የሙሽሪት እትብት ፡ አውሮፓ ተቋጥሮ
አሜሪካን ገባ ፡ ዘሎ ተንደርድሮ
አሰሱን ገሰሱን ፡ ከቶ በማሰሮ
ለግንቦት ልደታ ፡ ይቀቀላል ንፍሮ
ጭፈራው ዳንኪራው ፡ ደምቆ በከበሮ
ወይ ፡ ክህደት! ወይ ፡ ሞት ነው! መፈክር ዘንድሮ ፡፡

ድንቄም : ተቃዋሚ
ወያኔን : ከዳሚ
ትግልን : አዳካሚ
ሂደትን : አዝጋሚ
ለቃቅሞ : ቃራሚ ::

ወትሮ የማናውቀው : ዘመን አመጣሹ
የኦፌዴን : የኦብኮ : ልጠፉ ወራሹ
የአረና : ትግራይ : ወያኔ ትንሹ
እንደዚህ ነው : ትግል : የኋላ እየሸሹ
ሕዝብን እያስመቱ : ትግልን ቀልባሹ
ወጉ ነው : ምንደኛ : አድር ባይ ሹምባሹ
ከፋሽስት ወግኖ : አዙሮ ተኳሹ
የባንዳ ልጅ : ባንዳ : ሁሌም ተልከስካሹ ::

ቀድሞም : ባዬው ዘመን : በጣሊያን ወረራ
እንደ አርበኛ ታጥቆ : ፎክሮ እያቅራራ
ከሰው ተራ ገብቶ : ቀልጥፎ እያወራ
ጆሮ ሲጣባ አድሮ : ያርበኞችን ጎራ
ሹልክ ብሎ : ሄዶ : ጠላት የሚጠራ
አገሩን ያደማ : መንገድ እየመራ
ይሄው ተደገመ : ዛሬም : በኛ ተራ
በአንድነት ሰበብ : ክህደት ተሰራ ::

ድንቄም : ተቃዋሚ
ወያኔን : ከዳሚ
ትግልን : አዳካሚ
ሂደትን : አዝጋሚ
ለቃቅሞ : ቃራሚ ::

ትግል : መች ሆነና : ለሆዳም ቀርበታ
ከፓርላማ ጓሮ : ለመሸገ ሽፍታ
በቃላት ጦርነት : ቀድሞ ለሚፈታ

ተማርኮ ለሚሄድ ፡ ገና ፡ ሳይስብ ቃታ
ለሚርበደበደው ፡ በግልምጫ እይታ ፡፡

ምርጫ አስገቡን ብሎ ፡ ደጅ እየተጠና
ለውጥ ላያመጣ ፡ ዘንድሮም እንዳምና
ይወርድ ይመስል ፡ ስልጣን ፡ እንደ መና
ወያኔን ማኅልበት ፡ ተፈርቶ ፈተና
መታገልን ትቶ ፡ ሁል ግዜ ልመና ፡፡

በሆዱ የሚያስብ ፡ መቼ ፡ ጽናትን ያውቃል
ድል ቀርቦ ቢያየውም ፡ ለሱ ግን ይርቃል
በጊዜያዊ ተድላ ፡ ያገጣል ይስቃል
ሳይነካኩት ደርሶ ፡ ይሰነጣጠቃል
እሩቅ አይተልምም ፡ ባጭሩ ያበቃል
ፈጥኖ ሰማይ ደርሶ ፡ ፈጥኖ ግን ይወድቃል ፡፡

ድንቄም ፡ ተቃዋሚ
ወያኔን ፡ ከዳሚ
ትግልን ፡ አዳካሚ
ሂደትን ፡ አዝጋሚ
ለቃቅሞ ፡ ቃራሚ ፡፡

ንጋትና ጥራት ፡ እያደር እንዲሉ
እንኳን ለየላቸው ፡ ከሚወላውሉ
ሙሽሪትም ግንቦት ፡ አንድ ላይ ፡ ይዋሉ
ከወያኔ አብረው ፡ ሕዝብን ይበድሉ
ውጪ ነፍስ ፡ ግቢ ነፍስ ፡ ይፈራገጣሉ
ለስራቸው ዋጋ ፡ ባግባቡ ሳይከፍሉ
ሕዝብን የከዳች ነፍስ ፡ አትሄድ በቀላሉ
ከዚያ ይሰውራችሁ ፡ ክራራይሶ በሉ ፡፡

ታዛቢው